# ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ተብየው ባንዳ እንደ መለስ ዜናዊ በኢሳያስ አፈወርቂ ታግዞና በሻቢያ አጋሚዶ ኃይል ታጅቦ ወደ ሥልጣን ለመምጣት ከአገር ጠላት ጋር በምስጢር አሲሮ እየተዘጋጀ ነው

ከአስተዋይ በቀለ

**ልብ በል የኢትዮጵያ ሕዝብ !**

ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ተብየው የፖለቲካ ባንዳ፣ ሻቢያን የሚያምንና ኢሳያስ አፈወርቂን የሚያመልክ የፀረ_ ኢትዮጵያ ማኅበረ_ ባንዳ መሪ ነው።

ይህ በረከተ_ መርገም የተቆለለበት ርኩስ ሰው፣ ሥጋውም_ ነፍሱም ያልነጻ፣ የእግዚአብሔር ፀጋ የራቀው፣ ምላሱ አታላይ፣ሁከተኛና አባያ ከመሆኑ ጋር፤ የፖለቲካው ውሃቤ ነኝ ብሎ እንደ በሬ ቀንበር ውልቅ_ ውልቅ የሚል የባንዳ አቋም ይዞ የሐቀኛ ተቃዋሚዎችን ትግል ያሳደፈና ኢትዮጵያን የመከራ አውድማ ለማድረግ የቆመ ፀረ_ ሕዝብ ነው።

ርኩስ ስሙ በተነሳ ቁጥር ጥርሱን የነከሰበት ሰው ከሙብዛቱ የተነሳ፤ የማይንቀው፣ የማይጠላው፣ የማይረግመው፣ እንደ ቲቢያ የማይቆጥረው ጨርሶ የለም። ሁሉም አሰፍስፎ በጠላትነትና በንቀት ያየዋል።

ይህ ሰላቢ ባንዳ እኔ የምመራው ግንቦት 7 እያለ ቢፎክርም ፤ እንደ ከሰል ባቡር ፊቱን ያጠቆረና አፉን ያገማ ጥቀርሻ መትፋትና መከርፋት ተረፈው እንጂ፤ የተማመነበት ግንቦት 7 የትም ሳያደርሰው እንዳበቃለትና እዳለቀለት ተገንዝቦ፤ ሙሉ ተስፋውንና መመኪያውን በኢሳያስ አፈወርቂና በሻቢያ ኃይል ላይ አድርጎ በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ሕዝብና በግዛት ይዞታ ሕልውናችን ላይ ሴራ አቅዶ ይታያል።

ከግንቦት 7 ውድቀት ጋር ዶ/ር ብርሃኑ ነጋን በእጅጉ ያስፈራውና እንደ ሲቃ የተናነቀው ጥቁር ሥጋት የኢትዮጵያ ሕዝብ ፀረ_ ወያኔ ብሔራዊ አመፅ በስፋት መፈንጃውና እንደ ሱናሚ ማጥለቅለቂያው ስዓት እያራደፈ በየሰኮንዱ መቃረቡ ነው።

ይህ የማይቀረው ፀረ_ወያኔ ሕዝባዊ አመፅ እንደ እግዚአብሔር ቁጣ በኢትዮጵያ ምድር ሲከሰትና ሲፈስ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለማረጋገጥ ሲል ሕዝብ የራሱን መሪ፣ ድርጅታዊ ኃይልና ብሔራዊ አጀንዳ በሂደት ስለሚፈጥር እንደ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ አይነቱ ሕሊናው ያልጸዳ፣ የወያኔ አዋልድና የሻቢያ ቅጥረኛ ባንዳ እጣ ፈንታ ወደ ሥልጣን መምጣት ሳይሆን፤ አገርና ሕዝብ በመክዳት በብሔራዊ ትሪዝን ተይዞ በሕዝብ ጥይት መደብደብ ነው ።

ይችን የማትቀር ቀውጢ ቀን አበክሮ ለማምከንና ለማጨናገፍ ሲል ዶ/ር ብርሃኑ በወሰደው አቋም መሰረት የባድመ አፅመ_ ርስታችንና ወያኔ ከጐንደር የነጠቀውን የሁመራ ለም መሬት እንደ ልዋጭ_ ልዋጭ ዕቃ

ለኤርትራ  አቅርቦ፣ በምትኩ ሕዝባዊ ኃይል በሚል ሽፋን በሻቢያ ሠራዊት ታግዞና ታጅቦ እንደ መለስ ዜናዊ ወደ ሥልጣን ለመምጣት ከኢሳያስ ጋር በምስጢር በመስማማት ለዚህ ስትራቴጂውን፣ ዝርዝር ስልቱንና ወታደራዊ አፈጻጸሙን አሥመራ ላይ በወረቀት እያስነደፈና በካርታ እያሳለ መሆኑ ከጎቡዕ ምንጮች ተጠቁሟል ።

ይህን ያወቁ በየዳያስፖራው የከተሙ የሻቢያ ቦላሌ አፈኞችና የዛጉ ሰላዮች ደግሞ፣ ነፃ ልናወጣችሁ ነውና የሕዝብ አመፅ የሚለውን ቋንቋ ተውና ደማችሁ እንዳይጐርፍ፣ ሬሳችሁ እንዳይቆለል እጅ ስጡ እያሉ በኢትዮጵያዊያን ላይ ይደነፋሉ። ይህ አልበቃ ብሏቸው ትግሬን ቁልቋል እንዲግጥ ሌላውን ደግሞ እንደ አውዳመት ቅርጫ ሥጋ ቆራርጠን_ ከፋፍለን እናባላዋለን እያሉ ለዶ/ር ብርሃኑ ነጋ የሥልጣን ሴራ ከበሮ እየመቱለት ነው ።

**እስቲ እንግዲህ እናያለን !**

መቸም በኢትዮጵያ፣ በኢትዮጵያዊነትና በአረንጓዴ _ ቢጫ _ ቀይ ሰንደቅ ዓላማችን ላይ የማይቀፈቀፍና የማይሸረብ ሴራ የለም ። ነገር ግን አንዱም የኢትዮጵያን ሕዝብ ብሔራዊ አመፅ ከመቀስቀስና በአሸናፊነት ከመወጣት ልታግድ ከቶ አትችልም ። ምንጊዜም የኢትዮጵያ ሕዝብና ኢትዮጵያዊነት አሸናፊ ነው ።

ይህ በዚህ እንደለ፣ ይኸ የማኅበረ ባንዳ መሪ የሻቢያ ቅጥረኛ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ተብየው አገርህን፣ ዜግነትህን ፣ ሰንደቅ ዓላማህን ፣ መብትህን ፣ ሚስትህን ፣ ሴት ልጆችህን በፀራራ ፀሐይ በወሮበላነት የሚደፍር፣ ሃብትህን የሚዘርፍ ፣ ጐጆህን የሚያቃጥል፣ ዳቦና ሠላም የሚነሳህ፣አዘኔታና ርኅራሄ የማያሳይ **የሻቢያ አጋሚዶ ሠራዊት በሕዝባዊ ኃይል ሽፋን ሊያሰማራብህ** ያቀደብህ ለመሆኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉ አውቀህ ይህ ባንዳ ጠላትህ መሆኑን ተገንዘብ ።

**የኢትዮጵያ ጠላቶች ሁሉ ይደመሰሳሉ !**

**ሕዝብ ያሸንፋል !**